# የሐረማያ ዩኒቨርሲቲ የሙያ ጤንነትና ደህንነት አጠባበቅ፣
# የአደጋ መከላከያ መሳሪያዎችና ቁሳቁሶች አፈቃቀድና አፈጻጸም መመሪያ

ሐረማያ ዩኒቨርሲቲ
መስከረም 2007 ዓ.ም.

# ማውጫ

<u>ርዕስ</u> <u>ገጽ</u>

1.መግቢያ ....................................................................................................................................2
2.አጭር ርዕስ ................................................................................................................................3
3.የሙያ ጤንነትና ደህንነት አጠባበቅ፣ የአደጋ መከላከያ መሳሪያዎችና ቁሳቁሶች አፈ.ቃቀድና አፈጻጸም መመሪያ አላማ ..............................................................................................................................3
4.የሙያ ጤንነትና ደህንነት አጠባበቅ፣ የአደጋ መከላከያ መሳሪያዎችና ቁሳቁሶች አፈ.ቃቀድና አፈጻጸም መመሪያ አጠናን ስልት.........................................................................................................................3
5.ትርጓሜ.......................................................................................................................................3
6.የአደጋ መከላከያ መሳሪያዎችና ቁሳቁሶች የሚገባቸው የስራ መደቦች አፈ.ቃቀድ .........................................5
7.ሙያዊ ደንብ ልብሶች.....................................................................................................................6
8.የወተት አበል አፈ.ቃቀድ ................................................................................................................7
9.በስራ ላይ ለሚደርሱ አደጋዎችና በሽታዎች ስለሚሰጡ ህክምናዎችና ካሳዎች አፈጻጸም ...........................8
10.በስራ አከባቢና በሰራተኛ ጤንነትና ደህንነት አጠባበቅ የዩኒቨርሲቲው ባለድርሻ አካላት ያላቸው ሃላፊነትና ግዴታዎች ..........................................................................................................................9
11.በሀረማያ ዩኒቨርሲቲ የተፈቀዱ የአደጋ መከላከያ መሳሪያዎች በስራ መደብ.........................................11
12.የወተት አበል የተፈቀደላቸው የስራ መደቦች.........................................................................19

1. መግቢያ

የሐረማያ ዩኒቨርሲቲ በአዋጅ የተሰጠውን ተልዕኮ ለማስፈጸምና ራዕዩን ዕውን ለማድረግ የተለያዩ የለውጥ ትግበራ ዕቅዶችን በማውጣት እየተንቀሳቀሰ ይገኛል፡፡ በመሆኑም ዩኒቨርሲቲው የሰራተኞቹችን ደህንነት ለማስጠበቅና ሊደርሱ ከሚችሉ አደጋዎች የቅድመ ጥንቃቄ እርምጃዎችን በመውሰድ ሰራተኞች በተሰማሩበት ሙያ ተግባራቸውን በአግባቡ መወጣት እንዲችሉና የተሸለ ውጤት ውጤት እንዲያስመዘግቡ ተቋሙ የራሱ የሆነ ውስጣዊ የሙያ ጤንነትና ደህንነት አጠባበቅ፣ የአደጋ መከላከያ መሳሪያዎችና ቁሳቁሶች እንዲሁም ሙያዊ አለባበስ አፈ.ቃቀድና አፈጻጸም መመሪያ ማዘጋጀት አስፈላጊ በመሆኑ በፌደራል መንግስት ሰራተኞች አዋጅ 515/99 አንቀጽ 47-56 በተደነገገው መሰረትና በፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ነሐሴ 2000 ዓ.ም በተላለፈው የአደጋ መከላከያ መሳሪያዎችና ቁሳቁሶች ጥናት፣ አፈ.ቃቀድና አፈጻጸም መመሪያ በግልጽ እንደተደነገገው መስሪያ ቤቶች ካላቸው የስራ ጸባይ አንጻር የራሳቸው የሆነ የሙያ ጤንነትና ደህንነት አጠባበቅ፣ የአደጋ መከላከያ መሳሪያዎችና ቁሳቁሶች አፈ.ቃቀድና አፈጻጸም መመሪያ ማዘጋጀት እንደሚችሉ ስለሚፈቅድ ይህንኑ መነሻ በማድረግ ዩኒቨርሲቲያችን የሙያ ጤንነትና ደህንነት አጠባበቅ፣ የአደጋ መከላከያ መሳሪያዎችና ቁሳቁሶች አፈ.ቃቀድና አፈጻጸሙን በዚሁ መመሪያ መሰረት እንዲያከናውን ተስቦ የተዘጋጀ ነው፡፡

በዚህ መመሪያ በዩኒቨርሲቲው በተለያየ ሙያ ለሚሰሩ ሰረተኞች ከሙያቸው ባህሪ አንጻር የሚያስፈልጋቸውን የአደጋ መከላከያ ቁሳቁሶች አይነት ጥራት እንዲሁም በአንድ አመት ውስጥ ምን ያህል ጊዜ ቁሳቁሶቹ እንደሚታደሉ በግልጽ የተቀመጠ ሲሆን ሰራተኞች በስራ ቦታቸው ዩኒቨርሲቲውን ገላጭ በሆኑ አልባሳት እንዲሰማሩና የተወሰኑ የስራ አልባሳት ደግሞ በዩኒቨርሲቲው corporate color እና አርማ ታክሎባቸው እንዲታተሙ ለማድረግ ታሳቢ ተደርጎ መመሪያው ተዘጋጅቷል ፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ሰራተኞች የታደላቸውን የአደጋ መከላከያ በስራ ቦታቸው ባለመልበሳቸው ስለሚወሰዱት የዲሲፕሊን እርምጃዎች እንዲሁም የስራ አካባቢ ጤንነትንና ደህንነትን ለመጠበቅ አሰሪ ክፍሎች፣ ሰራተኞች፣ የሰው ኃብት ስራ አመራርና ልማት ዳይሬክቶሬትና ሌሎች የዩኒቨርሲቲው ባለድርሻ አካላት ያላቸውን ድርሻ በግልጽ እንዲያሳይ እና የአፈጻጸም መመሪያውን መሰረት በማድረግ ለመመሪያው ተፈጻሚነት ስላለው ድርሻ ግልጽ የሆነ አሰራር እንዲኖር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ይህ መመሪያ ተዘጋጅቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

**2. አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ የሃረማያ ዩኒቨርሲቲ የሙያ ጤንነትና ደህንነት አጠባበቅ፣ የአደጋ መከላከያ መሳሪያዎችና ቁሳቁሶች አፈቃቀድና አፈጻጸም መመሪያ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**3. የሙያ ጤንነትና ደህንነት አጠባበቅ፣ የአደጋ መከላከያ መሳሪያዎችና ቁሳቁሶች አፈቃቀድና አፈጻጸም መመሪያ አላማ**

ሀ. ዩኒቨርሲቲው ስትራቴጂክ ግቡን ሊያሳካ የሚችል ጤንነቱና ደህንነቱ የተጠበቀ ሰራተኛና የስራ አከባቢ ለመፍጠር

ለ. በዩኒቨርሲቲው የሚታደሉ የአደጋ መከላከያ መሳሪያዎችና ቁሳቁሶች ሰራተኞች ከሚሰሩት ሙያ አንጻር የሚደርሱ አደጋዎችን ለመከላከል የሚችሉ ለማድረግ

ሐ. ሰራተኞች በስራ ቦታቸው የሚለብሱት የስራ ልብሶች ዩኒቨርሲቲውን corporate color ገላጭ እንዲሆን ለማድረግ

መ፣ ከስራ ባህሪያቸው አንጻር የወተት አበል የሚያስፈልጋቸው የስራ መደቦች ለይቶ ግልጽ አሰራር እንዲኖር ለማድረግ

ሰ. የስራ አካባቢና የሰራተኞች ደህንነትና ጤንነት ለመጠበቅ በዩኒቨርሲቲው ያሉ የተለያዩ ባለድርሻ አካላትም ሚና በመለየት ግልጽ የሆነ አሰራር ለመፍጠር

ሸ. ከስራ ጋር ተያይዘው ለሚመጡ በሽታዎችና አደጋዎች ዩኒቨርሲቲው ስለሚሰጠው የህክምና አገልግሎቶችና ሌሎች ካሳዎች አፈጻጸም ወጥ በሆነ መልኩ ለማስተናገድ የሚያስችል አሰራር ለመፍጠር

ቀ. በስራ ቦታዎች የተሰጣቸውን የተለያዩ የአደጋ መከላከያ መሳሪያዎች ባልተጠቀሙ ሰራተኞች ላይ ስለሚደረጉ ክትትሎችና የዲሲፕሊን እርምጃዎች ግልጽ አሰራርን ለማስፈን በማሰብ ይህ መመሪያ ተዘጋጅቷል

**4. የሙያ ጤንነትና ደህንነት አጠባበቅ፣ የአደጋ መከላከያ መሳሪያዎችና ቁሳቁሶች አፈቃቀድና አፈጻጸም መመሪያ አጠናን ስልት**

1.1. የፌዴራል መንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/99 አንቀጽ 47-56 እና የፌዴራል ሰርቪስ የአደጋ መከላከያ መሳሪያዎችና ቁሳቁሶች ጥናት፣ አፈቃቀድና አፈጻጸም መመሪያ ነሐሴ 2000 ዓ.ም መሰረት በማድረግ

1.2. የተቋሙን ነባራዊ ሁኔታና በዩኒቨርሲቲው ስራ ላይ በዋሉ አዳዲስ የስራ መደቦችንና የአሰራር ሂደቶችን ከግንዛቤ በማስገባት ነው

**5. ትርጓሜ**

5.1. “**ዩኒቨርሲቲ**” ማለት የሀረማያ ዩኒቨርሲቲ ማለት ነው

5.2. **"በሥራ ላይ የሚደርስ ጉዳት"** ማለት በፌደራል መንግስት ሰራተኞች አዋጅ አንቀፅ 47/1/ ላይ እንደተደነገገው በሥራ ላይ የሚደርስ አደጋ ወይም በሥራ ምክንያት የሚመጣ በሽታ ነው፡፡

5.3. **"በሥራ ላይ የሚደርስ አደጋ"** ማለት በፌደራል መንግስት ሰራተኞች አዋጅ አንቀፅ 47/1 ላይ እንደተደነገገው የመንግስት ሠራተኛው መደበኛ ሥራውን በማከናወን ላይ እንዳለ ወይም ከሥራው ጋር በተያያዘ ምክንያት በአካሉ ወይም በአካሉ የተፈጥሮ ተግባር ላይ በድንገት የሚደርስ ጉዳት ነው፡፡

5.4. **"በሥራ ምክንያት የሚመጣ በሽታ"** ማለት በፌደራል መንግስት ሰራተኞች አዋጅ አንቀፅ 47/3/ ላይ እንደተደነገገው የመንግስት ሠራተኛው ከሚሰራው የሥራ ዓይነት ወይም ሥራውን ከሚያከናውንበት አካባቢ የተነሳ በሽታን ለሚያስከትሉ ሁኔታዎች ተጋልጦ በመቆየቱ ምክንያት የደረሰ የጤና መታወክ ሲሆን ሥራውን በሚያከናውንበት ቦታ የሚዛመቱና የሚይዙ ነዋሪ ወይም ተላላፊ በሽታዎችን አይጨምርም፡፡

5.5. **"የአካል ጉዳት" ማለት** በፌደራል መንግስት ሰራተኞች አዋጅ አንቀፅ 49 ላይ እንደተደነገገው የመሥራት ችሎታ መቀነስን ወይም ማጣትን በሚያስከትል ሁኔታ በሥራ ላይ የሚደርስ ጉዳት ነው፡፡

5.6. "ጊዜያዊ የአካል ጉዳት" ማለት በፌደራል መንግስት ሰራተኞች አዋጅ አንቀፅ 50 ላይ እንደተደነገገው ሠራተኛው ሥራውን ለተወሰነ ጊዜ በሙሉ ወይም በከፊል ለማከናወን እንዳይችል የሚያደረገው የአካል ጉዳት ነው፡፡

5.7. "ዘላቂ ከፊል የአካል ጉዳት" ማለት በፌደራል መንግስት ሰራተኞች አዋጅ አንቀፅ 51 ላይ እንደተመለከተው ጉዳት የደረሰበትን ሠራተኛ የመሥራት ችሎታ የሚቀንስ የማይድን በሥራ ላይ የሚደርስ ጉዳት ነው፡፡

5.8. "ዘላቂ ሙሉ የአካል ጉዳት" ማለት በፌደራል መንግስት ሰራተኞች አዋጅ አንቀፅ 52 ላይ እንደተመለከተው ጉዳት የደረሰበትን ሠራተኛ ማናቸውንም ደመወዝ የሚያስገኝ ሥራ ለመሥራት የሚከለክለው የማይድን በሥራ ላይ የሚደርስ ጉዳት ነው ፡፡

5.9. "የአደጋ መከላከያ መሣሪያዎችና ቁሳቁሶች" የሚባሉት ሠራተኛው ሥራውን የሚያከናውንበት ወቅት ከጤና ጠንቆችና አደጋዎች እራሱን ለመከላከል የሚለበሱ ፤ የሚደረጉ፤ የሚታሠሩ፤ የሚጠለቁ ወይም በጆሮዎች ውስጥ የሚሸጉጡ /የሚወተፉ/ የሥራ መሣሪያዎች ወይም የሥራ ልብሶች ናቸው ፡፡

5.10. "የሥራ አካባቢ ደህንነት" /Occupational safety /" ማለት አንድ ሠራተኛ በሥራ አካባቢው በሚገለገልባቸው የሥራ መሣሪያዎችና በሚከተላቸው የአሰራር ዘዴዎች ምክንያት ሊገጥሙት የሚችሉ አደጋዎችን የሚመለከት ነው፡፡

5.11. “የሥራ አካባቢ ጤንነት” /Occupational Health/ማለት ሠራተኛው ከሥራ አካባቢው ወይም ከተመደበበት የሥራ መደብ ባህርይ ሊመንጩ የሚችሉና በጤንነት ላይ ጉዳት ሊያደርሱ የሚችሉ ሁኔታዎችን ሚመለከት ነው፡፡

5.12. “የሥራ አካባቢ ደህንነትና ጤንነት” /Occupational safety and Health/” አጠባበቅ ማለት፡-

- የሠራተኞች አካላዊ አዕምሯዊ እና ማህበራዊ ደህንነታቸውን መንከባከብና ማሳደግ፤
- በሥራቸው ምክንያት ጤንነታቸው እንዳይጓደል መጠበቅና መከላከል፤
- ሠራተኞችን ከተፈጥሯዊ አካላቸው /physical/ እና አዕምሮአቸው /Mental/ ጋር በተጣጣመ መልኩ መድቦ ማሠራትና መከታታል ነው፡፡

## ክፍል ሁለት

### 6. የአደጋ መከላከያ መሳሪያዎችና ቁሳቁሶች የሚገባቸው የስራ መደቦች አፈቃቀድ

የአደጋ መከላከያ መሳሪያዎች ሰራተኞች ከሚሰሩት ስራ ወይም ከስራ አከባቢው የሚመነጩ የጤና ጠንቆች ለመከላከል የሚለበሱ፣ የሚደረጉ፣ የሚታሰሩ፣ የሚጠለቁ ወይም በጆሮ የሚወተፉ የስራ መሳሪያዎች ወይም አልባሳቶችን ያጠቃልላል፡፡

የመከላከያ ቁሳቁሶችም አፈቃቀድ ሰራተኞች ከሚሰሩት የስራ ጸባይ አንጻር ሊደርሱ ከሚችሉ አደጋዎችን መከላከል እንዲችሉና በስራ አከባቢዎችና አሰራር ሂደቶች ውስጥ ሊመነጩ ከሚችሉ ፊሲካል.ኬሚካል፣ባይሎጂካል ወዘተ ከሆኑ የጤና ጠንቆች መከላከል እንዲችሉ መሰረት ያደረገ ነው፡፡በመሆኑም የመከላከያ ቁሳቁሶቹ አግባብነታቸው ሰራተኞች በስራ ቦታ ላይ ከሚደርሱባቸው የተለያየ ባህሪ ካላቸው የጤና ጠንቆች (Occupational Hazards) ማለትም ፊዚካል ጠንቆች. /የመውደቅ፣ በስለት የመቆረጥ፣ ለፊዚካል ብናኞች መጋለጥ፣ የሬዲዮ አክቲቭ ጨረሮች መጋለጥ፣ ከፍተኛ ቅዝቃዜ፣ ከፍተኛ ሙቀት ወዘተ) ሲሆኑ ኬሚካል የጤና ጠንቆች ደግሞ የመትነን ባህሪ ያላቸው ውህዶች ከኬሚካሎች፣ የሚበኑ ኬሚካል ብናኞች የጸረ ተባይና አረም ኬሚካሎች የባይሎጂካል ጤና ጠንቅ ደግሞ ጊዜያቸው ካለፉ ተረፈ ምግብ ምርቶች፣ ከእንስሳት ወደ ሰው የሚተላለፉ በሽታዎች ለመከላከል እንዲቻሉ ሙያዊ ጥናት ላይ በመመስረት ነው፡፡

የስራ ቦታዎችንና አሰራሮችን ለይቶ ጥናት በማድረግ ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት ከተደረገበት በኋላ ተገቢውን ማስተካከያ በማከል የስራ አከባቢ ጤንነትና ደህንነት ባለሙያ በዩኒቨርሲቲው ላሉት የተለያዩ የስራ መደቦች የሚያስፈልጋቸውን የመከላከያ ቁሳቁሶችንና መሳሪያዎችን በማጤን ለይቶ እንዲፈቀዱ ለሰው ኃብት ስራ አመራርና ልማት ዳይሬክቶሬት ያቀርባል፣ ዳይሬክቶሬቱም ስራ ላይ እንዲውሉ በአስተዳደር ካውንስል በማቅረብ እንዲጸድቅ ያደርጋል፡፡

## 7. ሙያዊ ደንብ ልብሶች

ሙያዊ ደንብ ልብሶች ሰራተኞች ከሚሰሩት ሙያ ደንቦችና ድንጋጌዎች አንጻር የሚፈቀዱ ሃገር አቀፍ ወይም አለም አቀፍ ትርጉም ያላቸው ሙያዊ መገለጫ የአለባበስ ደንቦች ናቸው፡፡

የሙያዊ ደንብ ልብስ አወሳሰንና አፈቃቀድ መሰረታዊ ሙያው ከሚፈልጋቸው አፈቃቀድና አለባበስን መሰረት ያደረገ ሲሆን ዩኒቨርሲቲዉንም ለመግጽ በዩኒቨርሲቲው corporate color እንዲሁም እንዳስፈላጊነቱ የዩኒቨርሲቲው አርማ ታክሎባቸው ሊዘጋጁ ይችላሉ፡፡

በዩኒቨርሲቲውም የካምፓስ ፖሊስ ሙሉ ልብሶች (ኮትና ሱሪ)፣ የዩኒቨርሲቲው እንግዳ መቀበያ፣ የፕሮቶኮልና በዩኒቨርሲቲው ለሚከናወኑ የተለያዩ ክብረ በኣላት እንዲሁም ዩኒቨርስቲውን በተለያዩ መድረኮች ለመግለጽ የሚለበሱ የተለያዩ አልባት ሙያዊ ደንብ ልብስ ተብለው ሊመደቡ ይችላሉ፡፡

የደንብ ልብሶች አፈቃቀድና አጠቃቀም ሙያዊ ደንቦችን ባገናዘበ መልኩ ሲሆን እንደአስፈላጊነቱ ከሙያው አንጻር አሉታዊ ተጽእኖ በሌለው መልኩ በዩኒቨርሲቲው corporate color እና የዩኒቨርሲቲው አርማ ሊታከልባቸው ይችላል፤ አፈቃቀዳቸውም በስራ ክፍሉ ተጠንተው ለሰው ኃብት ስራ አመራርና ልማት ዳይሬክቶሬት ከቀረቡ በኋላ ዳይሬክቶሬቱ እንደአስፈላጊነቱ ለአስተዳደር ካውንስል በማቅረብ እንዲጸድቅ ያደርጋል፣ ለተፈጻሚነታቸውም ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፡፡

### 7.1. የሙያዊ ደንብ ልብሶች በጀት ምንጭና ግዢ

ከካምፓስ ፖሊስ ደንብ ልብሶች ውጭ ላሉ በዩኒቨርሲቲው ለተፈቀዱ ደንብ ልብሶች በጀት በአሰሪው ክፍል የሚያዝላቸው ሲሆን የግዢውን ሂደት እንዲከናወን በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ ወር ለሰው ኃብት ስራ አመራርና ልማት ዳይሬክቶሬት ይቀርባል፡፡

### 7.2. ሙያዊ የደንብ ልብሶች አቀራረብ

ለሁሉም የስራ መደቦች የሚሰጡ የደንብ ልብሶች የግዢ ፍላጎቶችን መሰረት በማድረግ የዩኒቨርሲቲው የማዕከላዊ የግዢ ንዑስ የስራ ሂደት የተጠየቁትን ልብሶች በሙሉ በሰራተኛው መጠን (Size) ተገዝተውና ተሰፍተው እንዲቀርቡ ይደረጋል፡፡

## 8. የወተት አበል አፈቃቀድ

ሰራተኞች ከሚሰሩት ስራ ባህሪና ከስራ አከባቢ በባህሪያቸው ለጤና ጠንቆች ለተጋለጡ ለስራ መደቦቹ የወተት አበል ይፈቀድላቸዋል፡፡

የወተት አበል ለሚፈቀድላቸው የስራ መደቦች በሙያ ጤንነትና ደህንነት ባለሙያ ከስራው አንጻርና ከስራ አከባቢው ካሉት ነባራዊ ሁኔታዎች በመነሳት ሰራተኞች በባህሪያቸው የመትነን ባህሪ ካላቸው ኬሚካሎች ፣አሲራማነት፣ጉዳት ሊያስከትሉ ከሚችሉ ራዲኦ አክቲቭ ጨረሮች እንዲሁም ሌሎች የጤና ጠንቅ ናቸው ለሚባሉ ስራዎችና የአሰራር ሁኔታዎችን በቅርብ በማጤን የወተት አበል እንዲፈቀድላቸው ለሰው ኃብት ስራ አመራርና ልማት ዳይሬክቶሬት የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል ዳይሬክቶሬቱም እንደአስፈላጊነቱ ተፈጻሚ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡

ኤክስ ሬይ ቴክኒሺያንና ከባድ ህትመት መሳሪያዎች ቴክኒሽያን ሙያ ስራ መደብ ለሚሰሩ ባለሙያዎች በቀን አንድ ሊትር ወተት በአይነት የሚፈቀድላቸው ሲሆን ከነዚህ መደብ ውጪ ላሉ ሰራተኞች አበሉ በወር ብር 80 በደመወዛቸው ላይ ታክሎ ይከፈላቸዋል፡፡

### 8.1. የወተት አበል በጀት ምንጭ

የሰው ኃብት ስራ አመራርና ልማት ዳይሬክቶሬት በሚይዘው የሰው ኃብት እቅድ መሰረት እንዲሁም አበሉ የሚገባቸው መደብ ላይ በነባርነት ለሚሰሩ ሰራተኞች ለሚከፈል የወተት አበል በበጀት አመቱ እቅድ ይይዛል ክፍያውም እንዲፈጸም ለሚመለከተው ክፍል መመሪያ ይሰጣል፡፡

### 8.2. የደንብ ልብስና የአደጋ መከላከያ ባለመጠቀም የሚወሰዱ የዲሲፕሊን እርምጃዎች

ሀ/ ማንኛውም ሰራተኛ የደንብ ልብስ እንዲለብስ ከተሰጠው በኋላ በስራ ቦታው ላይ የተሰጠውን የደንብ ልብስ ሳይለብስ ቢገኝ በፌደራል መንግስት ሰራተኞች አዋጅ 515/99 አንቀጽ 68 ቁጥር 1 መሰረት ከባድ የዲሲፕሊን ግድፈት እንደፈጸመ ተቆጥሮ ባለው አሰራር እርምጃ ይወሰድበታል፡፡

ለ/ ማንኛውም ሰራተኛ ለስራ የተሰጠውን የአደጋ መከላከያ አልባሳት ባለመጠቀም ለሚደርስበት ጉዳት በፌደራል መንግስት ሰራተኞች አዋጅ 515/99 አንቀጽ 47 ቁጥር 5 መሰረት ለሚደርስበት ጉዳት ዩኒቨርሲቲው ተጠያቂ ማድረግ አይችልም፡፡

## ክፍል ሶስት

### 9. በስራ ላይ ለሚደርሱ አደጋዎችና በሽታዎች ስለሚሰጡ ህክምናዎችና ካሳዎች አፈጻጸም

በመንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/99 እንደተቀመጠው አንድ የመንግስት ሰራተኛ በስራው ምክንያት ለሚደርስበት አደጋና በሽታ እንደየደረጃቸው የህክምናና የካሳ ክፍያዎች በግልጽ የተደነገገ ቢሆንም ማንኛውም የህክምናና አገልግሎትና የካሳ ክፍያዎች ለመፈጸም ሊሟሉ የሚገባቸው ቅድመ ሆኔታዎች አሉ፡፡

በሥራ ላይ የሚደርስ አደጋ ማለት በአንቀፅ 47/1 ላይ እንደተደነገገው የመንግስት ሠራተኛው መደበኛ ሥራውን በማከናወን ላይ እንዳለ ወይም ከሥራው ጋር በተያያዘ ምክንያት በአካሉ ወይም በአካሉ የተፈጥሮ ተግባር ላይ በድንገት የሚደርስ ጉዳት ሲሆን በአንቀጽ 47 በተገለጸው መልኩ አደጋዎች ሲከሰቱ የሚከተሉት ቅድመ ሁኔታዎች መሟላት አለባቸው፡፡

### 9.1. በስራ ለደረሱ አደጋዎችና በሽታዎች ህክምናዎችና የካሳ ክፍያዎች ለሚፈጸም መሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች

በስራ ቦታ ለደረሱ አደጋዎችና በሽታዎች ሪፖርት ለማድረግ በተዘጋጀ ቅጽ በአሰሪው ክፍል ሃላፊና በሶስት ምስክሮች ተሞልቶና ተፈርሞ አደጋው/በሽታው ከተከሰተ ከሶስት ቀን ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ተሞልቶ ለሰው ኃብት ስራ አመራርና ልማት ዳይሬክቶሬት ሪፖርት መደረግ አለበት፡፡

አደጋው/ በሽታው የደረሰበት ሰራተኛ የህክምና አገልግሎት ዩኒቨርሲቲው በአጋርነት በመረጣቸው የጤና ተቋማት አገልግሎቱ እንዲሰጠው የድጋፍ ደብዳቤ በመያዝ ወደ ተቋማቱ መሄድ አለበት፡፡

ማንኛውም የህክምና አገልግሎት የሚሰጠው ዩኒቨርሲቲው በመረጣቸው የጤና ተቋማት ወይም ተቋማቱ በሚያዙትና በሚጽፉት ሪፈራል መሰረት ብቻ ነው፡፡

### 9.2. የህክምና ወጪ አሸፋፈን

- ሰራተኞች በጤና ተቋማቱ የድጋፍ ደብዳቤ ይዘው በመሄድ ለተቋማቱ ግቢው በሚሸፍነው ወጪ አገልግሎቱን ያገኛሉ
- ለህክምና የሚወጡ የትራንስፖርትና በተቋማቱ ለሌሉ በተቋሙ የሚታዘዙ የመድሃኒት ግዢዎችና ሌሎች አገልግሎቶች ሰራተኛው በሚያቀርበው ህጋዊ ደረሰኝ ክፍያ ይፈጸማል

- ከዩኒቨርሲቲው እውቅና ውጪ ለሚፈጸሙ ማንኛውም የህክምና አገልግሎቶች ወጪ በግቢው አይሸፈንም

10. **በስራ አከባቢና በሰራተኛ ጤንነትና ደህንነት አጠባበቅ የዩኒቨርሲቲው ባለድርሻ አካላት ያላቸው ሃላፊነትና ግዴታዎች**

የስራ አከባቢና የሰራተኞች ጤንነትና ደህንነተ የማስጠበቅ በዩኒቨርሲቲው ሰራተኞች እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት የሚከተሉት ሃላፊነትና ግዴታዎች ይኖራቸዋል፡፡

10.1. የሰው ኃብት ስራ አመራርና ልማት ዳይሬክቶሬት

ሀ/ የሠራተኞችን ደህንነትና ጤንነት ለመጠበቅ የወጡ ሕጎችን እና መመሪያዎችን በዩኒቨርሲቲው ተፈጻሚ እንዲሆኑ ለአስተዳደር ካውንስል በማቅረብ ተፈጻሚ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡

ለ/ ለሰራተኞች ደህንነትና ጤንነት ለመጠበቅ የተሰጡትን የሥራ አካባቢ ደህንነትና ጤንነት መከላከያ መሣሪያዎችና ቁሳቁሶች በአግባቡ በጥቅም ላይ ስለመዋላቸው የሚከታተል ኮሚቴ ያቋቅማል ፡፡

ሐ/ በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ያሉትን የስራ አከባቢ ጤንነትና ደህንነት መመሪያዎች አፈጻጸማቸውን ይከታተላል መሻሻል ሲኖርባቸውም ከሚመለከታቸው ጋር በመሆን እንዲሻሻሉ ያደርጋል፡፡

መ/ የሥራ አካባቢ ደህንነትና ጤንነት አጠባበቅን የተመለከቱ ጉዳዮች በባለሙያ ተጠንተው ሲቀርቡለት ውሳኔ ይሰጣል፡፡

ሰ/ በሥራ አካባቢ ደህንነትና ጤንነት አጠባበቅ ዙሪያ ከሠራተኞች የሚቅርቡ ቅሬታዎችን ተቀብሎ የማጣራቱን ተግባር እንዲያከናውን ለባለሙያው ይመራል፤ ከባለሙያ በሚቀርበው ሪፖርት ላይ ውሣኔ ይሰጣል፤ ወይም እንደአስፈላጊነቱ ለበላይ ኃላፊ በማቅረብ ሲወስን እንዲፈፀም ያደርጋል፡፡

10.2. የሥራ አከባቢ ጤንነትና ደህንነትና አጠባበቅ ባለሙያ /Occupational Health and safety officer / ዋና ዋና ተግባራትና ኃላፊነት

ሀ/ የሥራ ቦታዎች መሣሪያዎች እና የአሠራር ዘዴዎች በሠራተኞች ደህንነትና ጤንነት ላይ አደጋ ሚያስከትሉ መሆናቸውን ያረጋግጣል፡፡

ለ/ ሠራተኞች የሚሠሩት ሥራ ሊያስከትልባቸው ስለሚችለው አደጋ እንዲሁም በጤንነት ላይ የሚደርስ ጉዳትን ለማሰወገድ ስለሚያስፈልግው ጥንቃቄ ተገቢውን ሥልጠና ለሠራተኞች ይሰጣል፡፡

ሐ/ የሥራ አካባቢ ደህንነትና ጤንነት መጠበቂያና መከላከያ መሣሪያዎችና ቁሳቁሶችን አጥንቶ ያቀርባል፤ ሲፈቀድም ሥራ ለይ እንዲውል ያደርጋል፡፡

መ/ በሥራ ላይ የደረሱ አደጋዎችንና በሽታዎችን በተመለከተ አስፈላጊው እርምጃ በወቅቱ እንዲወስድ ያደርጋል፤ መረጃዎችንም መዝግቦ ይይዛል፡፡

ሰራተኞች የተፈቀድላቸውን የአደጋ መከላከያ ቁሳቁሶች በወቅቱ እንዲቀርብላቸው ክትትል ያደርጋል የታደሉ ቁሳቁሶም በአግባቡ ስራ ላይ ስለመዋላቸው ክትትል በማድረግ ተፈጻሚ

ባላደረጉ የስራ ክፍሎችና ሰራተኞች እርምጃ እንዲወሰድ ለሰው ኃብት ስራ አመራርና ልማት ዳይሬክቶሬት ያቀርባል

10.3. የአሰሪ ክፍል ኃላፊዎች ግዴታና ሃላፊነት

ሀ. በክፍሉ የሚሰሩ ሰራተኞች የተሰጣቸውን ማንኛውም የስራ አከባቢ ደህንነትና ጠየንነት መከላከያ መሳሪያዎች በአግባቡ እንደጠቀሙ ያደርጋል

ለ. ሰራተኞች የተሰጣቸውን አደጋ መከላከያ ቁሳቁሶች ሳይጠቀሙ ወደ ስራ አለመሰማራታቸውን ያረጋግጣል ተፈጻሚ ባላደረጉ ሰራተኞችም እርምጃ ይወስዳል

ሐ. የሥራ አካባቢ ደህንነትና ጤንነት አጠባበቅን በተመለከተ በየጊዜው ቁጥጥር ከሚያደርጉ ተቆጣጣሪዎች ለሚቀርብለት ጥያቄ መረጃና መልስ ይሰጣል ፡፡

መ. በተደጋጋሚ የተሰጣቸውን የአደጋ መከላከያ በማይጠቀሙ ሰራተኞች ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ ለሰው ኃብት ስራ አመራርና ልማት ዳይሬክቶሬት ሪፖርት ያደርጋል

ሰ. በስራ ክፍሉ በሰራተኞች የሚደርሱ አደጋዎችን በወቅቱ ሪፖርት ያደርጋል

ረ. በስራ ክፍሉ ከስራ አከባቢ ጤንነትና ደህንነት ጋር የተያያዙ ብሎ የሚያምናቸውን የስልጠና ፍላጎቶች ለሰው ኃብት ስራ አመራርና ልማት ዳይሬክቶሬት ሪፖርት ያደርጋል

10.4. የዩኒቨርሲቲው ሠራተኛ ግዴታ

ሀ/ የሠራተኞችን ደህንነትና ጤንነት ለመጠበቅ የወጡ ሕጎችን እና መመሪያዎችን ያከብራል፡፡

ለ/ የራሱን ወይም የሌሎችን ደህንነትና ጤንነት ለመጠበቅ የተሰጡትን የሥራ አካባቢ ደህንነትና ጤንነት መከላከያ መሣሪያዎችና ቁሳቁሶች በአግባቡ በጥቅም ላይ ያውላል፡፡

ሐ/ የሥራ ላይ አደጋ ወይም የጤንነት ችግር ሊያደርስ ይችላል ብሎ ያመነውንና በራሱ ሊያስወግደው ያልቻለውን ማንኛውንም ሁኔታ ወይም ስጋት ለስራ ክፍሉ ሃላፊ፣ ወይም ለስራ አከባቢ ጤንነትና ደህንነት ባለሙያ ወዲያውኑ ያሳውቃል፡፡

መ/ መሥሪያ ቤቱ በየጊዜው ሚያወጣቸውን የሥራ አካባቢ ደህንነትና ጤንነት አጠባበቅ መመሪያዎችን ይከታተላል፣ በሚሰጡ ሥልጠናዎች ላይም ይሳተፋል፡፡

ሰ/ የሥራ አካባቢ ደህንነትና ጤንነት አጠባበቅን በተመለከተ በየጊዜው ቁጥጥር ከሚያደርጉ ተቆጣጣሪዎች ለሚቀርብለት ጥያቄ መረጃና መልስ ይሰጣል ፡፡

## ክፍል 4

### 11. በሀረማያ ዩኒቨርሲቲ የተፈቀዱ የአደጋ መከላከያ መሳሪያዎች በስራ መደብ

| ተ.ቁ | የስራ መደቡ መጠሪያ | የተፈቀዱ የአደጋ መከላከያዎች ዝርዝር | ጥራት | ከለር | ብዛት/በ ዓመት | ተጨማሪ መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1. | ሾፌር V እስከ VII | ሙሉ ኮትና ሱሪ | ፖሊስተር | ጥቁር ሰማያዊ | 2 | |
| | | ሸሚዝ | ፖሊስተር | ጥቁር ሰማያዊ | 2 | |
| | | አጭር ቡትስ ቆዳ ጫማ | ሙሉ ቆዳ | ጥቁር | 2 | |
| 2. | ሾፌር I እስከ ሾፌር III | ሙሉ ኮትና ሱሪ | ፖሊስተር | ጥቁር ሰማያዊ | 2 | |
| | | ሸሚዝ | ፖሊስተር | ውሃ አረንጓዴ | 2 | |
| | | አጭር ቆዳ ጫማ | ሙሉ ቆዳ | ጥቁር | 2 | |
| 3. | መካኒክ III | ቱታ | ፖሊስተር | ውሃ አረንጓዴ | 2 | የግቢው አርማ ታትሞበት |
| | | ጓንት | ሙሉ ቆዳ | | 4 | |
| | | አጭር ቡትስ ቆዳ ጫማ | ሙሉ ቆዳ | ጥቁር | 2 | |
| 4. | መካኒክ II<br>መካኒክ I | አጭር ቡትስ ቆዳ ጫማ | ሙሉ ቆዳ | ጥቁር | 2 | |
| | | ቱታ | ፖሊስተር | ውሃ አረንጓዴ | 2 | የግቢው አርማ ታትሞበት |
| | | ጓንት | ሙሉ ቆዳ | | 4 | |
| 5. | ረዳት ሾፌር | ሙሉ ኮትና ሱሪ | ፖሊስተር | ጥቁር ሰማያዊ | 2 | |
| | | ሸሚዝ | ፖሊስተር | ጥቁር ሰማያዊ | 2 | |
| | | ቱታ | ፖሊስተር | ውሃ አረንጓዴ | 1 | የግቢው አርማ ታትሞበት |
| | | ጋወን | ፖሊስተር | ውሃ አረንጓዴ | 1 | የግቢው አርማ ታትሞበት |
| | | አጭር ቡትስ ቆዳ ጫማ | ሙሉ ቆዳ | ጥቁር | 2 | |
| 6. | ጎሚስታ | አጭር ቡትስ ቆዳ ጫማ | ሙሉ ቆዳ | ጥቁር | 2 | |
| | | ጓንት | ሙሉ ቆዳ | | 4 | |
| | | ቱታ | ፖሊስተር | አረንጓዴ | 1 | የግቢው አርማ ታትሞበት |
| 7. | ነዳጅና ቅባት አዳይ | የጨርቅ ጓንት | ከጥጥ የተሰራ | | 2 | |
| | | ማስክ | ፕላስቲክ | | 4 | |
| | | ሙሉ ሽርጥ | ፖሊስተር | ውሃ አረንጓዴ | 2 | የግቢው አርማ ታትሞበት |
| | | ቡትስ ቆዳ ጫማ | ሙሉ ቆዳ | ጥቁር | 2 | |
| | | ቱታ | ፖሊስተር | ውሃ አረንጓዴ | 1 | የግቢው አርማ ታትሞበት |
| 8. | ረዳት ነዳጅና ቅባት አዳይ | ጋወን | ፖሊስተር | ውሃ አረንጓዴ | 1 | የግቢው አርማ ታትሞበት |
| | | የጨርቅ ጓንት | ከጥጥ የተሰራ | | 2 | |

| ተ.ቁ | የስራ መደቡ መጠሪያ | የተፈቀዱ የአደጋ መከላከያዎች ዝርዝር | ጥራት | ከለር | ብዛት/በ ዓመት | ተጨማሪ መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ማስክ | ፕላስቲክ | | 2 | |
| | | ሙሉ ሽርጥ | ፖሊስተር | ውሃ አረንጓዴ | 1 | የግቢው አርማ ታትሞበት |
| | | ቡትስ ቆዳ ጫማ | ሙሉ ቆዳ | ጥቁር | 2 | |
| 9. | አውቶ ኤሌክትሪሺያን | ቡትስ ቆዳ ጫማ | ሙሉ ቆዳ | ጥቁር | 1 | |
| | | ቱታ | ፖሊስተር | ውሃ አረንጓዴ | 1 | የግቢው አርማ ታትሞበት |
| | | የጨርቅ ጓንት | ከጥጥ የተሰራ | | 2 | |
| | | ማስክ | ፕላስቲክ | | 2 | |
| | | ቡትስ ቆዳ ጫማ | ሙሉ ቆዳ | ጥቁር | 2 | |
| 10. | የተሽከርካሪ ቦዲ ሥራዎች ሠራተኛ | ቡትስ ቆዳ ጫማ | ሙሉ ቆዳ | ጥቁር | 1 | |
| | | ቱታ | ፖሊስተር | ውሃ አረንጓዴ | 1 | የግቢው አርማ ታትሞበት |
| | | ጋወን | ፖሊስተር | ውሃ አረንጓዴ | 1 | የግቢው አርማ ታትሞበት |
| | | የጨርቅ ጓንት | ከጥጥ የተሰራ | | 2 | |
| 11. | የተሽከርካሪ ባትሪ ቴክኒሽያን | አጭር ቡትስ ቆዳ ጫማ | ሙሉ ቆዳ | ጥቁር | 2 | |
| | | ቱታ | ፖሊስተር | ውሃ አረንጓዴ | 2 | የግቢው አርማ ታትሞበት |
| | | ፕላስቲክ ጓንት | ፕላስቲክ | | 2 | |
| | | ፕላስቲክ ሽርጥ | ፕላስቲክ | | 1 | |
| 12. | የተሽከርካሪ እጥበት ሥራዎች ሠራተኛና ወልዋይ | ቱታ | ፖሊስተር | ውሃ አረንጓዴ | 2 | የግቢው አርማ ታትሞበት |
| | | ቡትስ ጫማ | ፕላስቲክ | አረንጓዴ | 1 | |
| | | አጭር ቡትስ ቆዳ ጫማ | ሙሉ ቆዳ | ጥቁር | 1 | |
| 13. | የጀኔረተር ኦፕሬተር | አጭር ቡትስ ቆዳ ጫማ | ሙሉ ቆዳ | ጥቁር | 2 | |
| | | ቱታ | ፖሊስተር | ውሃ አረንጓዴ | 2 | የግቢው አርማ ታትሞበት |
| | | ፕላስቲክ ጓንት | ፕላስቲክ | | 2 | |
| 14. | የውሀ ፓምፕ ኦፕሬተር | አጭር ቡትስ ቆዳ ጫማ | ሙሉ ቆዳ | ጥቁር | 2 | |
| | | ቱታ | ፖሊስተር | ውሃ አረንጓዴ | 2 | የግቢው አርማ ታትሞበት |
| | | ቡትስ ጫማ | ፕላስቲክ | | 2 | |
| 15. | ቦይለር ኦፕሬተር | አጭር ቡትስ ቆዳ ጫማ | ሙሉ ቆዳ | ጥቁር | 2 | |
| | | ቱታ | ፖሊስተር | አረንጓዴ | 2 | የግቢው አርማ ታትሞበት |
| | | ቡትስ ጫማ | ላስቲክ | አረንጓዴ | 2 | |

| ተ.ቁ | የስራ መደቡ መጠሪያ | የተፈቀዱ የአደጋ መከላከያዎች ዝርዝር | ጥራት | ከለር | ብዛት/በ ዓመት | ተጨማሪ መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የጨርቅ ጓንት | | | 2 | |
| 16. | የኤሌክትሪክ ሥራ ጥገና ሠራተኛ | አጭር ቡትስ ቆዳ ጫማ | ሙሉ ቆዳ | ጥቁር | 2 | |
| | | ቱታ | ፖሊስተር | ቀይ | 2 | የግቢው አርማ ታትሞበት |
| | | የኤሌክትሪክ ጓንት | | | 2 | |
| 17. | ኤሌክትሪሽያንና ከፍተኛ ኤሌክትሪሽያን | አጭር ቡትስ ቆዳ ጫማ | ሙሉ ቆዳ | ጥቁር | 2 | |
| | | ጋወን | ፖሊስተር | ቀይ | 2 | የግቢው አርማ ታትሞበት |
| | | የኤሌክትሪክ ጓንት | | | 2 | |
| 18. | ማብሰያና ማቀዝቀዣ ዕቃዎች ጠጋኝ | ጋወን | ፖሊስተር | ቀይ | 1 | የግቢው አርማ ታትሞበት |
| | | ቱታ | ካኪ | ቀይ | 1 | የግቢው አርማ ታትሞበት |
| | | የኤሌክትሪክ ጓንት | | | 2 | |
| | | አጭር ቡትስ ቆዳ ጫማ | ሙሉ ቆዳ | ጥቁር | 2 | |
| 19. | ኤሌክትሮኒክ ቴክኒሻን | ጋወን | ፖሊስተር | ቀይ | 2 | የግቢው አርማ ታትሞበት |
| | | አጭር ቡትስ ቆዳ ጫማ | ሙሉ ቆዳ | ጥቁር | 2 | |
| 20. | ሲቪል መሐንዲስ ΙΙ | ጋወን | ፖሊስተር | ቀይ | 2 | የግቢው አርማ ታትሞበት |
| | | ሄልሜት | ፕላስቲክ | ሰማያዊ | 1 | |
| | | ሴፍቲ ቆዳ ጫማ | ሙሉ ቆዳ | ጥቁር | 1 | |
| 21. | ኤሌክትሪካል መሐንዲስ ΙΙ | ጋወን | ፖሊስተር | ቀይ | 1 | የግቢው አርማ ታትሞበት |
| | | የኤሌክትሪክ ጓንት | | | 1 | |
| | | ሄልሜት | ፕላስቲክ | ሰማያዊ | 1 | |
| | | ሴፍቲ ቆዳ ጫማ | ሙሉ ቆዳ | ጥቁር | 1 | |
| 22. | መካኒካል መሐንዲስ ΙΙ | ጋወን | ፖሊስተር | ቀይ | 2 | የግቢው አርማ ታትሞበት |
| | | ሄልሜት | ፕላስቲክ | ሰማያዊ | 1 | |
| | | ሴፍቲ ቆዳ ጫማ | ሙሉ ቆዳ | ጥቁር | 1 | |
| 23. | ህንጻ ጥገና ሠራተኛ /ግንበኛ/ | ቱታ | ፖሊስተር | አረንጓዴ | 2 | የግቢው አርማ ታትሞበት |
| | | የመስክ ቆብ | ካኪ | አረንጓዴ | 1 | |
| | | የጨርቅ ጓንት | ከጥጥ የተሰራ | | 2 | |
| | | አጭር ቡትስ ቆዳ ጫማ | ሙሉ ቆዳ | ጥቁር | 2 | |
| 24. | የእንጨት ሥራ ጥገና ሠራተኛ | የጨርቅ ጓንት | ከጥጥ የተሰራ | | 2 | |
| | | ሄልሜት | ፕላስቲክ | ብጫ | 1 | |
| | | አጭር ቡትስ ቆዳ ጫማ | ሙሉ ቆዳ | ጥቁር | 2 | |

| ተ.ቁ | የስራ መደቡ መጠሪያ | የተፈቀዱ የአደጋ መከላከያዎች ዝርዝር | ጥራት | ከለር | ብዛት/በ ዓመት | ተጨማሪ መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ቱታ | ፖሊስተር | ቢጫ | 2 | የግቢው አርማ ታትሞበት |
| | | ጉግል | ፕላስቲክ | | 2 | |
| 25. | በያጅ | የጨርቅ ጓንት | ከጥጥ የተሰራ | | 4 | |
| | | የቆዳ ጓንት | ሙሉ ቆዳ | | 4 | |
| | | የብየዳ መነጽር | ፕላስቲክ | ጥቁር | 2 | |
| | | ቡትስ ቆዳ ጫማ | ሙሉ ቆዳ | ጥቁር | 2 | |
| | | ቱታ | ፖሊስተር | ቢጫ | 2 | የግቢው አርማ ታትሞበት |
| 26. | የውሀቧንቧ መስመር ሠራተኛ | ቱታ | ፖሊስተር | አረንጓዴ | 2 | የግቢው አርማ ታትሞበት |
| | | አጭር ቡትስ ቆዳ ጫማ | ሙሉ ቆዳ | ጥቁር | 2 | |
| | | ፕላስቲክ ቡትስ ጫማ | ፕላስቲክ | አረንጓዴ | 1 | |
| 27. | የቆሻሻ መስመር ቧንቧ ሠራተኛ | ቱታ | ፖሊስተር | አረንጓዴ | 2 | የግቢው አርማ ታትሞበት |
| | | ቡትስ ቆዳ ጫማ | ሙሉ ቆዳ | ጥቁር | 2 | |
| | | ፕላስቲክ ቡትስ ጫማ | ፕላስቲክ | አረንጓዴ | 2 | |
| | | ፕላስቲክ ጓንት | ፕላስቲክ | | 4 | |
| 28. | ከፍተኛ ቀለም ቀቢ ሰራና ቀለም ቀቢ ሰራተኛ | የጨርቅ ጓንት | ከጥጥ የተሰራ | | 2 | |
| | | ማስክ | የጨርቅ | | 2 | |
| | | ቱታ | ፖሊስተር | ውሃ አረንጓዴ | 2 | የግቢው አርማ ታትሞበት |
| | | ቡትስ ጫማ | ፕላስቲክ | | 2 | |
| | | አጭር ቡትስ ቆዳ ጫማ | ሙሉ ቆዳ | ጥቁር | 2 | |
| 29. | የህትመትና ማተሚያ ማሽን ኦፕሬተር | ማስክ | የጨርቅ | | 2 | |
| | | የጨርቅ ጓንት | ከጥጥ የተሰራ | | 4 | |
| | | አጭር ቡትስ ቆዳ ጫማ | ሙሉ ቆዳ | ጥቁር | 2 | |
| | | ጋወን | ፖሊስተር | ጥቁር ሰማያዊ | 2 | የግቢው አርማ ታትሞበት |
| 30. | የህትመት ካሜራና ፍልም ዝግጅት መለስተኛ ባለሙያ | የጨርቅ ጓንት | ከጥጥ የተሰራ | | 4 | |
| | | አጭር ቡትስ ቆዳ ጫማ | ሙሉ ቆዳ | ጥቁር | 2 | |
| | | ጋወን | ፖሊስተር | ጥቁር ሰማያዊ | 2 | የግቢው አርማ ታትሞበት |
| | | ማስክ | የጨርቅ | | 2 | |
| 31. | የህትመት ቤት የሎጅስቲክ ሠራተኛ | ማስክ | የጨርቅ | | 2 | |
| | | ጋወን | ፖሊስተር | ጥቁር ሰማያዊ | 2 | የግቢው አርማ ታትሞበት |
| | | አጭር ቡትስ ቆዳ ጫማ | ሙሉ ቆዳ | ጥቁር | 2 | |
| 32. | የፎቶ ኮፒና | ማስክ | የጨርቅ | | 2 | |

| ተ.ቁ | የስራ መደቡ መጠሪያ | የተፈቀዱ የአደጋ መከላከያዎች ዝርዝር | ጥራት | ከለር | ብዛት/በ ዓመት | ተጨማሪ መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ማባዣ ሰራተኛ የመልቀምና የመጠረዝ ሠራተኛ | ጋወን | ፖሊስተር | ጥቁር ሰማያዊ | 2 | የግቢው አርማ ታትሞበት |
| 33. | እንጨት መልማይ ከርካሚና አትክልተኛ ሳር ተንከባካቢ | የጨርቅ ጓንት | ከጥጥ የተሰራ | | 2 | |
| | | አጭር ቆዳ ጫማ | ሙሉ ቆዳ | ጥቁር | 2 | |
| | | ቱታ | ፖሊስተር | ውሃ አረንጓዴ | 2 | የግቢው አርማ ታትሞበት |
| | | ሸሚዝና ጉርድ/ሱሪ | ፖሊስተር | ውኃ ሰማያዊ | 2 | |
| | | ሸሚዝ | | | 2 | |
| 34. | የምድረ ግቢ ውበት ሰራተኛ | ቱታ | ፖሊስተር | ውሃ አረንጓዴ | 1 | የግቢው አርማ ታትሞበት |
| | | ሽርጥ | ፖሊስተር | | 1 | |
| | | የጨርቅ ጓንት | ከጥጥ የተሰራ | | 2 | |
| | | አጭር ቆዳ ጫማ | ከቆዳ የተሰራ | | 2 | |
| | | ሸሚዝና ጉርድ/ሱሪ | ፖሊስተር | | 2 | |
| | | ሸሚዝ | | | 2 | |
| 35. | ጽዳት ሠራተኛ I እና II | ጋወን | ፖሊስተር | ሽሮ ከለር | 1 | የግቢው አርማ ታትሞበት |
| | | ሙሉ ሽርጥ | ፖሊስተር | | 1 | |
| | | ጓንት | ፕላስቲክ | | 4 | |
| | | ሸሚዝና ጉርድ/ሱሪ | ፖሊስተር | | 2 | |
| | | ሸሚዝ | | | 2 | |
| 36. | ቆሻሻ አስወጋጅ I እና II | ፕላስቲክ ቡትስ ጫማ | ፕላስቲክ | | 2 | |
| | | ቱታ | ፖሊስተር | ሽሮ ከለር | 2 | የግቢው አርማ ታትሞበት |
| | | አጭር ቆዳ ጫማ | ሙሉ ቆዳ | | 2 | |
| | | ፕላስቲክ ጓንት | ፕላስቲክ | | 4 | |
| | | ፕላስቲክ ሽርጥ | ፕላስቲክ | | 2 | |
| | | ሸሚዝና ጉርድ/ሱሪ | ፖሊስተር | | 2 | |
| | | ሸሚዝ | | | 2 | |
| 37. | የዩኒቨርሲቲ ፖሊስ | ረዥም ቡትስ ቆዳ ጫማ | ሙሉ ቆዳ | ጥቁር | 1 | |
| | | አጭር ቆዳ ጫማ | ሙሉ ቆዳ | ጥቁር | 1 | |
| | | የሱፍ ካፖርት | ሙሉ በሙሉ ሱፍ | ጥቁር | በሁለት አመት 1 | |
| | | የእጅ ባትሪ | | | 1 | |

| ተ.ቁ | የስራ መደቡ መጠሪያ | የተፈቀዱ የአደጋ መከላከያዎች ዝርዝር | ጥራት | ከለር | ብዛት/በ ዓመት | ተጨማሪ መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የዝናብ ልብስ | ፕላስቲክ | | 1 | |
| | | ሙሉ ኮትና ሱሪ/ኮትናጉርድ | ፖሊስተር | ውሃ አረንጓዴ | 2 | |
| | | የጨርቅ ኮፍያ/ባለማይካ ቆብ | ፖሊስተር | አረንጓዴ | 2 | |
| | | ሸሚዝ | ከጥጥና ሴንቴቲክ የተሠራ | ውሃ ሰመያዊ | 2 | |
| 38. | ትራፊክ ፖሊስ | ረዥም ቡትስ ቆዳ ጫማ | ሙሉ ቆዳ | ጥቁር | 1 | |
| | | ሙሉ ልብስ /ኮትና ሱሪ | ፖሊስተር | ውሃ አረንጓዴ | 2 | የግቢው አርማ ታትሞበት |
| | | የትራፊክ ሰደርያ | ፖሊስተር | አረንጓዴ | 2 | |
| | | የትራፊክ ኮፍያ | ፖሊስተር | ነጭ | 2 | |
| | | አጭር ቆዳ ጫማ | ሙሉ ቆዳ | ጥቁር | 1 | |
| 39. | የጉልበት ሠራተኛ | ቱታ | ፖሊስተር | ጥቁር ሰማያዊ | 2 | የግቢው አርማ ታትሞበት |
| | | አጭር ቡትስ ቆዳ ጫማ | ሙሉ ቆዳ | | 2 | |
| | | ሙሉ ሽርጥ | ፖሊስተር | | 1 | |
| 40. | የማዕድ ቤት አደራጅ፣ እንጀራ ጋጋሪ፣ ሊጥ አቡኪና ዳቦ ጋጋሪ፣ ዋና ምግብ አብሳይ፣ ምግብ አብሳይና ወጥ ቤት ሠራተኛ | ኮትና ሱሪ/ጉርድ/ቀሚስ | ፖሊስተር | | 2 | |
| | | አጭር ቆዳ ጫማ | ሙሉ ቆዳ | ጥቁር | 2 | |
| | | ጋወን | ፖሊስተር | ነጭ | 2 | |
| | | ሙሉ ሽርጥ | ፖሊስተር | ቡኒ | 2 | |
| | | የጨርቅ ቆብ | ፖሊስተር | ነጭ | 2 | |
| | | ሸሚዝ | ፖሊስተር | | 2 | |
| 41. | ሥጋ ቆራጭ | ሙሉ ሽርጥ | ፖሊስተር | ቡኒ | 2 | |
| | | አጭር ቆዳ ጫማ | ሙሉ ቆዳ | ጥቁር | 2 | |
| | | የጨርቅ ቆብ | ፖሊስተር | ነጭ | 4 | |
| | | ጋወን | ፖሊስተር | ነጭ | 2 | |
| 42. | ልብስ አጣቢ | የጨርቅ ቆብ | ፖሊስተር | ነጭ | 2 | |
| | | ጋወን | ፖሊስተር | ነጭ | 1 | |
| | | ቡትስ ጫማ | ፕላስቲክ | | 2 | |
| 43. | የምግብ ጥሬ እቃዎች መጋዘን ሰራተኛ | የጨርቅ ቆብ | ፖሊስተር | ነጭ | 2 | |
| | | ጋወን | ፖሊስተር | ነጭ | 2 | |
| | | አጭር ቆዳ ጫማ | ሙሉ ቆዳ | ጥቁር | 2 | |
| 44. | የቡና ማሽን ኦፕሬተር | ሙሉ ሽርጥ | ፖሊስተር | ቡኒ | 1 | |
| | | የጨርቅ ቆብ | ፖሊስተር | ነጭ | 2 | |
| | | ጋወን | ፖሊስተር | ነጭ | 2 | |

| ተ.ቁ | የስራ መደቡ መጠሪያ | የተፈቀዱ የአደጋ መከላከያዎች ዝርዝር | ጥራት | ከለር | ብዛት/በ ዓመት | ተጨማሪ መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | አጭር ቆዳ ጫማ | ሙሉ ቆዳ | ጥቁር | 2 | |
| 45. | የምግብ ቤት አስተባባሪ ምግብ አስተናጋጅ | ጋወን | ፖሊስተር | ነጭ | 2 | |
| | | ሙሉ ልብስ /ኮትና ጉርድ/ሱሪ/ቀሚስ | ፖሊስተር | | 2 | |
| | | አጭር ቆዳ ጫማ | ሙሉ ቆዳ | ጥቁር | 2 | |
| | | ሸሚዝ | ፖሊስተር | | 2 | |
| 46. | የተማሪዎች መኝታ ቤት ተቆጣጣሪ | ጋወን | ፖሊስተር | ውሃ ሰማያዊ | 2 | የግቢው አርማ ታትሞበት |
| 47. | የምግብ ቤት ኃላፊ ሼፍ | ነጭ ቆብ | ፖሊስተር | ነጭ | 4 | |
| | | ሙሉ ሸርጥ | ፖሊስተር | ነጭ | 2 | |
| | | ጋወን | ፖሊስተር | ነጭ | 2 | |
| 48. | አራጅና ብልት አውጪ | ጋወን | ፖሊስተር | ነጭ | 2 | |
| | | ረዥም ቡትስ ቆዳ ጫማ | ሙሉ ቆዳ | ጥቁር | 2 | |
| | | ፕላስቲክ ሸርጥ | ፕላስቲክ | | 2 | |
| 49. | የምግብ ቤት ሥነ ስርዓት ተቆጣጣሪ/ቲከር/ | ጋወን | ፖሊስተር | ነጭ | 2 | |
| 50. | አንፋሽና የወፍጮ ቤት ሠራተኛ | ሙሉ ሸርጥ | ፖሊስተር | ቡኒ | 1 | |
| | | የጨርቅ ቆብ | ፖሊስተር | ቡኒ | 2 | |
| | | የጨርቅ ማስክ | ፖሊስተር | | 2 | |
| | | ቱታ | ፖሊስተር | ቡኒ | 2 | |
| 51. | የላውንደሪ ማሽን ኦፕሬተር | የጨርቅ ጓንት | ፖሊስተር | | 1 | |
| | | ቱታ | ፖሊስተር | ቡኒ | 1 | |
| 52. | ተላላኪ | ጃኬትና ጉርድ ቀሚስ | ጥጥናድብልቅ | ውሃ አረንጓዴ | 2 | |
| | | አጭር ቆዳ ጫማ | | ጥቁር | 2 | |
| 53. | የመማሪያ ክፍሎች አስተዳዳሪ | ጋወን | ፖሊስተር | ውሃ አረንጓዴ | 1 | |
| 54. | የግብርና ልማትና | አጭር ቆዳ ጫማ | ሙሉ ቆዳ | ጥቁር | 1 | |
| 55. | የምርምር ጥበቃ ሰራተኞች | ኮትና ሱሪ | | ውሃ አረንጓዴ | | |
| | | ረጅም ቡትስ ጫማ | | ጥቁር | 1 | |
| 56. | የዶሮ ቤት ሰራተኛ | ቱታ | | | 2 | |
| | | ላስቲክ ቡትስ ጫማ | | | 1 | |
| | | አጭር የቆዳ ጫማ | | | 2 | |
| 57. | ለጤና ባለሞያዎች | ጋወን | ፖሊስተር | ነጭ | 2 | |
| 58. | ወተት አላቢ | ቱታ | ካኪ | ውሃ አረንጓዴ | 2 | |

| ተ.ቁ | የስራ መደቡ መጠሪያ | የተፈቀዱ የአደጋ መከላከያዎች ዝርዝር | ጥራት | ከለር | ብዛት/በ ዓመት | ተጨማሪ መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሸርጥ ነጭ | ካኪ | ነጭ | 1 | |
| | | የጨርቅ ቆብ | ጥጥ | | 2 | |
| | | ላስቲክ ቡትስ ጫማ | | | 2 | |
| 59. | ከብት እረኛና ተንከባካቢ | ኮትና ሱሪ/ጉርድ/ቀሚስ | ፖሊስተር | ውሃ አረንጓዴ | 2 | |
| | | ቱታ | ካኪ | አረንጓዴ | 2 | |
| | | የመስክ ቆብ | ካኪ | | 1 | |
| | | የዝናብ ልብስ በሁለት ዓመት አንድ | | ጥቁር | 1 | |
| | | አጭር ቆዳ ጫማ | ሙሉ ቆዳ | | 2 | |
| | | ላስቲክ ቡትስ ጫማ | ላስቲክ | | 2 | |
| 60. | የመድሐኒት ርጭት ሰራተኛ | ቡትስ ጫማ | ፕላስቲክ | | 2 | |
| | | ቱታ | ውሃ አረንጓዴ | | 2 | |
| 61. | የቤተ መጽሐፍ ሠራተኛ | ጋወን | ካኪ | ነጭ | 2 | |

12. **የወተት አበል የተፈቀደላቸው የስራ መደቦች**

| ተ.ቁ | የስራ መደቡ መጠሪያ | የወተት አበል ዓይነት | ምርመራ |
|---|---|---|---|
| 1. | X ray ቴክኒሺያን | 1 ሊትር በስራ ቀን | በዓይነት |
| 2. | ከባድ የህትመት ማሽን ባለሙያ | 1 ሊትር በስራ ቀን | በዓይነት |
| 3. | የቆሻሻ መስመር ቧንቧ ሠራተኛ | ብር 80 በወር | |
| 4. | ከፍተኛ ቀለም ቀቢ | ብር 80 በወር | |
| 5. | ቀለም ቀቢ | ብር 80 በወር | |
| 6. | የፎቶ ኮፒና ማባዣ ሰራተኛ | ብር 80 በወር | |
| 7. | የመልቀምና የመጠረዝ ሠራተኛ | ብር 80 በወር | |
| 8. | የህትመት ካሜራና ፊልም ዝግጅት መለስተኛ ባለሙያ | ብር 80 በወር | |
| 9. | የኬሚካል ላብራቶሪ ባለሙያ | ብር 80 በወር | |
| 10. | አንፋሽ | ብር 80 በወር | |
| 11. | የወፍጮ ቤት ሰራተኛ | ብር 80 በወር | |

